# ያልገባን ምንድነው ያልተረዳነው?

### ከበላይ መታፈሪያ

ኢትዮጵያ እጅግ በአስከፊ የጭቆና ሥርዓት ከወደቀች(ከተያዘች) ረዘም ያለ ጊዜ አለፈ። አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ በአንድነቷ፣ በታሪኳ፣ በትውልድ የሚኮራ ይህን መገንዘብ፣ ማወቅ፣ የአገርን ዳር ድንበር፣ ሃብትና ቅርሱን መጠበቅም አለበት።

ኢትዮጵያ ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወዲህ ሕልውናዋ እና የሕዝቧ የወደፊት ዕድሏ ትልቅ አደጋ ላይ የወደቀበት ጊዜ ቢኖር ዛሬ በወያኔ/ኢህዴግ ወያኔአዊ አምባገነን አስተዳደር ነው።

ሕዝባዊ ሐርነት ትግራይ(ሕወሓት) ወያኔ እና ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሻዕቢያ) እጅና ጓንት ሆነው በጥፋት መልክተኝነት ከወረሯት ጊዜ አንስቶ አገሪቱን በማፈራረስና በብሔር ሸንሽነው ሕዝቧን ወደ ማያባራ የርስበርስ ጦርነት ለመክተት በአገር ውስጥ የብሔር መርዝን ሆነ ብለው እረጩ። ወያኔ ይዞት የተነሳው ትግራይን ያለ ትግራይ ሕዝብ ፈቃድና አወንታ ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የትግራይ ብሔራዊ ሪፖሊክን (Tigray Nationalism) ለመመስረት ፀረ-ኢትዮጵያ ፀረ-አማራ አቋምን አንግቦ የትግራይን ኢትዮጵያዊነት ከታሪክ ማኅደር አውጥቶና ለይተው ለትግራይ ነፃነት ብሎም አያሌ ኢትዮጵያኖችን ደም ያፈሰሰ የገዳይ ቡድን ነው።

ኢትዮጵያን በሚጠሉ በውጭ አገሮች ተዘጋጅተውና ታግዘው ከታሪካዊ ጠላቶች ጋር በማበር አጥብቀው ሲታገሏት የቆዩና ያሉ ጠላቶች ናቸው። የወያኔ ጎጠኛ ዘረኛነት ትግራይን ነፃ ለማውጣት ዓላማው አድርጎ በመንሳት ገና ከጅምሩ ኅብረ ብሔር የሆኑ ድርጅቶችን፣ ፓርቲዎችን በትግራይ ውስጥ እንዳይዘዋወሩ እንዳይኖሩ በማድረግ አጥፍቷል፣ ገሎአል። ከትግራይም እንዲወጡ በማሳደድ ጥቃት አድርሷል(ኢዴኅን፣ ኢህአፓ፣ መኤሶን ወዘተ…) ሌሎችንም በምርኮ በመውሰድ የወያኔዊ ሥርዓት ተከታይ በማድረግ ተጠቅሞባቸዋል እየተጠቀመም ነው። ወያኔ ብሔሮችን በብሔር ስም አደራጅቶ የኢትዮጵያን ማነስና፣ መጥፋት ዓላማው ያደረገና የሚመኝ ለዚህም ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርግ ሲሆን ስራና ተግባሩ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ያሳየው ትብብር ታሪካዊ ምስክሮች ናቸው።

በምስራቅ ኢትዮጵያ የሱማሌ ተስፋፊዎች ኢትዮጵያን እንዲወጉ የውጊያውም ተባባሪ እንደነበረ ዓለም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ኤርትራ ከእናት አገሯ ኢትዮጵያ እንድትገነጠል ከሻዓብያ ጦር ጋር በመተባበር ለኤርትራ መገንጠል አባሪነቱን ዋናና ቀጥተኛ ተቀዳሚ

አጋዥ በመሆን የኢትዮጵያ ጦር ኃይል እንዲዳከምና እንዲሸነፍ ያልተደረገ ሸፍጥና ተንኮል የለም፣ ብሎም ለማስገንጠል ከፍተኛ ሚናን ተጫውቶ አስገንጥሏል።

ወያኔ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ የመጣ ወራሪ ጠላት ነው። ለአንድነት ሳይሆን ለመበታተን፣ ለመገንባት ሳይሆን ለማፈራረስ፣ ለልማት ሳይሆን ለመዝረፍ፣ ለማፋቀር ሳይሆን ለማጣላት፣ለማናከስ ለማቀራረብ ሳይሆን ለማራራቅ፣ ለማለያየት የመጣ ወያኔያዊ ርዕዮተ ሥርዓት ፀረ-ኅብረተሰብ ባህሪ ያለው ጠባብ፣ ጎጠኛ፣ ጥላቻ፣ ሸፍጥንና ተንኮልን መመሪያው ያደረገ ሃብት የሚያከማች የጥቅም ቡድን ኃይል ነው።

አምባ ገነናዊ፣ አስመሳይ ዲሞክራሲና ሰላምን አራማጅ፣ ከፋፋይነት፣ ዘረኝነትን ጭካኔንና አፋኝነት የኃይል መስሪያው አድርጎ በውሸትና በይሉኝታ ቢስነት በተገኘው መንገድ ጥቅሙንና ሥልጣኑን የሚጠብቅ ወያኔያዊ ሥርዓት ነው። ለአገርና ለሕዝብ ታሪክ ከበሬታ የማይሰጥ ለሰው ርኅራኄን የማያሳይ በስልጣንና በዘረፋ ለመቆየት ማንኛውንም ነገር ከማድረግ የማይቆጠብ፣ የራሱን የቡድን አካል እንኳን ሳይቀር እንቅፋትና ጥቅሙን የማይጠብቁ ከመሰሉት ሰውን እንደ ዕቃ ተጠቅሞ የሚጥል፣ የሚገል፣ የሚያስር (Human Disposable) ሥርዓት የያዘ ነው።

ወያኔ ጥላቻን፣ አለመቻቻልን ልዩነት ላይ አጎልቶ በማሳየት ፀረ- አንድነት ሥርዓት ሲሆን የእያንዳንዱ ብሔር ፍላጎት በጥቅም ላይ የተመሰረተ ሆኖ ብሔሮች ጥቅማቸውን ለማግኘትና ለማስጠበቅ ከፖለቲካ ኃይሉ (ከወያኔ) ርዳታ በመሻት ፍራቻቸውንና ደህንነታቸውን ይፈልጋሉ ከሚል ያተኮረ የሥርዓት ዓይነት ነው።

የኅብረተሰብን ብልጽግና የሚፈልግ ሥርዓት ያለው መንግሥት የብሔርን መታወቂያ በቅድሚያ በመስጠት ብሔርን በመለያየት አትዮጵያን ለመግዛት ይሞክራል?

መለስና ቡድኖቹ (ወያኔዎች) ለምን የብሔር መመሪያን (Policy) በመንደፍና በማራመድ ኢትዮጵያን ሊገዙ ፈለጉ?

በእኔ አስተሳሰብ የማይካድ እሉታ አለው። የሕዝብ - ኢትዮጵያዊ ኅብረ ብሔራዊ ስሜት እንዲናጋ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊነት ስሜት (Ethiopian Nationalsim) እንዲጠፋ የብሔሮች አገር እንድትሆን ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲቻል ነው።

የትግራይን ብሔር ነፃነት ፖለቲካ በማራመድና ለትግራይ ኤኮኖሚ ርዳታን በማሳየት የትግራይንና ሌሎች ብሔሮችን በማቃረን (በተለይ ከአማራው) እና በትግራይ ላይ ጥላቻ እንዲመጣ በማድረግ ከትግራይ የድጋፍ ርዳታ ለማግኘት። ትግራያን ደግሞ ይህን ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የወያኔን ጥበቃ፣ የደህንነት ዋስትና ይሻሉ ከሚል ሲሆን ሌላው

ደግሞ ኢትዮጵያ ብሔራዊነት የለም፣ ኖሮም አያውቅ ስለሚሉና እያንዳንዱ ብሔር የራሱ ኤኮኖሚና እድገት ይኑረው ብለው ነው ብለው የሚያምኑ ግለሰቦች አሉ።

ነገር ግን ከፋፍሎና አዳክሞ ለመግዛት ከሌሎችም ብሔሮች ሃብት ለትግራያን እንዲደርስ(እንዲሄድ) ለመዝረፍ ታስቦ ነው።

አቶ መለስና ቡድኖቹ (ወያኔአዊ ሥርዓት) የኢትዮጵያን አንድነት ማጥፋትና ብሎም የትግራይን ብሔራዊ ሪፖብሊክ ለመመስረት የተነደፈ ዕቅድ እና ዓላማ ይዘው የተነሱ ስለሆነ ብሔርን እንደ ዋና መሳሪያ በማድረግ ትግራይ ኢትዮጵያዊያን (በአንድነት የሚያምኑ) ማሳመኛ ይሆን ዘንድ ብሔሮች በቋንቋ ልዩነት ላይ ተመስርተው ቢደራጁ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊነትን ማፍረስ እንደሚቻልና አዳክሞም ለመግዛት፣ ሸንሽኖ፣ ለመሸጥ የፋሽስታዊ ጥላቻ ባሕሪ ያለው ቡድን ነው።

ሕወሓት ወያኔ መሪዎች ይዘው የተነሱት ዓላማ ትግራያን ብሔራዊ ሪፐብሊክ (Tigray Nationalism Republic) ሆኖና ኖሮ የማያውቅ አስደናቂ ነገር ነው። ለብዙ ሺህ ዓመታት አብረውና በአንድነት የባህልም ሆነ የፖለቲካ ትስስር ከአማራው ጋር ሆነ ከሌሎች ያላቸውን በመለየትና ትግራያን የተለየ መታወቂያ አድርጐ መስጠትና ኢትዮጵያዊነትን መንጠቅ በታሪካችን ቦታ የለውም ብሎም ትግራያንን ተጠቅሞ አማራውን ለማጥፋት ማሰብና መጠራት ለአማራው ብቻ ሳይሆን ለትግራያንም የሚያሳዝን ሳይሆን እንደማይቀር እምነት አለኝ። ለዚህም ነው አያሌ ታላላቅ አዛውንቶች ለኢትዮጵያ አንድነት የተዋደቁና በታሪኳም የሚኮሩትን ሰብስበው ለታሪክ እንዳይተርፍ አድርገው የገደሏቸው። ይህን ታዛቢዎች በገሃድና በቁጭት ይናገራሉ፣ ያወራሉ። ትግራያን ኢትዮጵያዊ ሳይሆኑ ማን ኢትዮጵያዊ ይሆናል? ታሪክ ይፍረደው ለትግራይ ሕዝብ እተወዋለሁ።

ሕዋሓት ወያኔ የተጠመቀው የተማረውን፣ አማራውንና የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነትን ማጥፋት ነው።

ወያኔ በስልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጠ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጨቆን እና ረግጦ ለመግዛት ኃይልን ዋና መሳሪያ አድርጎ ይዞታል። ወያኔ ይህን የጨቋኝነት ባህሪውን በብሔር ፖሊሲ መመሪያ ላይ በማድረግ ግልጽና አጥፊነቱን በጉልህ በብሔር ላይ መስርቶ ኢትዮጵያን አላውቅም በማለት የብሔር ብሔራዊነትን በማስቀደም ሕዝብን ከሕዝብ ጋር አናክሶ ለመለያየት ሞከረ። ግን አልሆነም። በብሔረሰቦች መሐል የጋራ የሆነ ግንኙነት፣ ባሕል ታሪክ፣ ኅብረት እንደሌለ ትግሬውን ከአማራው፣ ከኦሮሞው፣ ከጉራጌው እንዲሁም ከሌሎች ሁሉ ላለማመሳሰል ተሞከረ። ሁሉም የጋራ የሆነ የላቸውም አማራው በኃይል አንድ

አድርጎ ከመያዙ በስተቀር በማለት ታወጀ። ኢትዮጵያዊያን የብሔሮች እስር ቤት አሏት (ዛሬ እነሱ ጠቅላላ ኢትዮጵያን ሰፊ የእስር ቤት አገር አርገዋታል)

ከወራሪ ከዚህ የበለጠ ከፋፍለህ ግዛው ምን ይጠበቃል! ክፍለ አገሮችን በማጥቃትና በወረራ የመጣ ኃይል ለነዋሪው ሕዝብ ተመሳሳይነት፣ አንድነት፣ ባህል ሆነ ታሪክ የሌለው መጥ ወራሪ፤ ለመግዛት ይህን ከማለት አይቆጠብም አያስደንቅም። (ኤርትራዊ Mercenary)

ኢትዮጵያ የብዙ ሺህ ዓመት የጋርዮሽ ታሪክ ያላት አገር መሆኗን መካድና አለማወቃቸውን አረጋገጡልን። ወያኔ ይህን የውጭ የወራሪ ባህሪ በማሳየት ወደ አንድ ያልታወቀ አገር መጥቶ የጭካኔና አረመኔነት ተግባሩን ያለ ፍራቻና ያለ ዕፍረት ተያያዘው።

ብሔርን ከብሔር በማጣላት የራሳቸውን ፍላጎትና ዓላማ ለሟሟላት የኢትዮጵያ ብሔራዊነት መግደል አማራጭ ኃይላቸው እንደሆነ አደረጉት። በጥቅም ላይ የተመሰረተ ተራና ኋላ ቀር የሆነ የጥላቻን፣ የፍራሃትንና ያለመተማመንን ለብሔር ምሁራን መቀስቀሻና ዋና የችግር መንስኤ እንዲሆን አጥብቀው በመያዝ ብሔርን ከብሔር (ከአማራው) በማጣላት መርዙን በስፋት ረጩት።

የኢትዮጵያን ብሔራዊነት በመጥላት ለመሆኑ መረጃው በ1997 ግንቦት ምርጫ እና የቅንጅት ማሸነፉን በጉልበትና በአመጽ ቀምቶ እስከ አሁን በስልጣን ላይ ተቀምጦ ወደፊትም እያሰበ ያለ አገር፣ ወገን አጥፊ ቡድን ነው። ይህን ማንም አይክደውም። ለዚህ ነው የመለስ ቡድን በየጊዜው በተደጋጋሚ የከፈለውን ከፍሎ ማንኛውንም ተንኮል በመጠቀም የደህንነቱን ኃይል አጎልብቶ፣ እንቅፋት የሆነውን ጠንካራ ኢትዮጵያዊ አንድነት ያላቸውን ግለሰቦችም ሆነ ፓርቲዎች (መኢአድ) ለማጥፋት ለማዳከም ሲጥር የሚታየው የሚገደለው፣ የሚታሰረው፣ ከአገር የሚሰደደው የዚህ ሀቅ ምስክሮች ናቸው።

በዚህ ዓይነት አቶ መለስና ቡድኑ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን ሊገቱና ሊያቀዘቅዙ ሊያዳፉት ይሞክራሉ። በዚህ ጥረትም ይህን መሰል ጦርነት በስራ ላይ እንዲውል እያደረገ ነው።

በቅርቡ የወያኔ መሪ አቶ መለስ ወያኔአዊ ሥርዓት የተመሰረተበትን 35ኛ ዓመት ሲያከብሩ ለቡድኑና ለደጋፊዎቻቸው ትግራይ ውስጥ የተናገረው (ጠቅላላ የትግራይን ሕዝብ አይወክልም ብዬ አምናለሁ) ተቀዋሚ ፓርቲዎች የወያኔ “ጠላቶች” ናቸው ብለው አረጋግጠዋል። ከዚያም አልፎ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ “ጭቃ” ነው ሲሉ ተሰምተዋል።

ይህ አነጋገርና ድፍረት ለኛ በእውነት ኢትዮጵያን ለምንወድና ልንጠብቃት ልንከባከባት ግዴታች ኃላፊነታችንም ለሆነው ኢትዮጵያዊ ያልተረዳነው ያልገባን ምን ይሆን? ወያኔ ማነው? ወያኔ ምንድነው?

- አድዋ ሰዎች ባንዳዎች በዘርና በጋብቻ የተያዙ
- ችግር ያለባቸው፣ ተለጣፊዎች፣ ሌቦች
- በኢትዮጵያ ላይ (በቤተሰቡ) ወይንም በራሱ ችግር ያለው
- በገንዘብ የተገዙ ለራስ ጥቅም የሚኖሩ
- ለአገር ለወገን ደንታ የሌላቸው ታሪክ ቢሶች ናቸው።

የወያኔን ማንና ምንነት ጠቅለል ላድርገውና ያልገባንን ያልተረዳነውን ለማወቅና አቋማችንን ማንነታችንን በተግባር እንድናሳይ ይሁን።
በኢትዮጵያዊነታችን የሚጠላን፣ ሊያጠፋን ከተዋጋንና ከወረረን፤ እየዘረፈን እየጨቆነንም በአገራችን ላይ ከተቆናጠጠ 18 ዓመት አለፈው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ያጠፋው፣ የበደለው ያልገባው ኢትዮጵያዊ አለ ብሎ ማመን ያስቸግራል (በወያኔ ሥርዓት የተጠመቁ ባንዳዎች ካልሆን በስተቀር)

1. ወያኔ የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገሮችን እየተዋጋ፤ እየወረረ መጥቶ መናገሻ ከተማችን አዲስ አበባን እንደያዘ አቶ መለስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተናገረው ከአሁን በኋላ **"እንደፈለጋችሁ ሁኑ"** እኛን ለመዋጋት (ወያኔን) የምትፈልጉ መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደንታ እንደሌለው እንደማይፈራን፣ እንደማያከብረን እና ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚጠላ መሆኑን በፌዝ አምባገነናዊነቱ ነገረን።
2. **"ሰንደቅ ዓላማችንን ጨርቅ"** ነው በማለት የነፃነት፣ የአንድነት፣ የኅብረት፣የታሪክ ክብርና መኩሪያችንን አርማ አያሌ ሺህ ዓመታት ታግለው ያቆዩልንን የኩራታችን መታወቂያን ዝቅ አድርጎ በመገመትና በማሰብ ለመቀየርም ብዙ ጥረት እንዳደረገና አሁንም እየተሞከረ ነው።
3. **ኅብረትና አንድነት** በሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ድርጅቶች ላይ ዘመቻ እያካሄደ ሲሆን በሃይማኖትም ላይ የተመሰረቱ ልዩነቶችንና ግጭቶችን እያበረታታ ነው።
4. አገሪቱ አንድ ሰፊ እስር ቤት ወይንም **የእስረኞች አገር ሆናለች።** *"ሰላም ሰፈነ ዲሞክራሲ"* የሚል አስመሳይ ፕሮፓጋንዳ ቢነዙም ሕዝቡ በአገሩ ሰላማዊ ኑሮውና ሥራውን ለማንቀሳቀስ እንዳይችል መንገዶች ታጥረው መዘዋወር አቅቶታል።

5. **የፍርድ ቤቶች፣ የፖሊሲ መዋቅሮች ፈርሰው ሕዝቡ በሕግ መዳኘቱ ቀርቶ በመሳሪያ ኃይል** በጎጠኛ በአንድ ብሔር እየተገዛ ነው።
6. ወያኔ ትግራይን ለመገንጠል **የነፃ አውጭ ዓላማ ይዞ** የተነሳ እስከ አሁንም ይህን ዓላማ ያልቀየረ እና ሌሎች ብሔረሰቦች ይህን ዓላማ እንዲከተሉ በሕግ ያፀደቀና (አንቀጽ 39) የሚያበረታታ ነው።
7. ሕዝብን ከሕዝብ (ብሔርን ከብሔር) ካናከሰ በኋላ **የኢትዮጵያ አካል ለሁለት ተከፍሎ** የኤርትራ ሕዝብ በተለይ (የአፋርና የኩናማ) በቃል ኪዳን አብሮ በኢትዮጵያዊነት ሲታገልና ሲደማ የኖረ ያለ ፍላጎቱና ፈቃዱ እንዲገነጠል ተደረገ። ኢትዮጵያ የውሃ በሯ ተዘግቶ ያለ ወደብ ቀረች።
8. **ኢትዮጵያ ወዳጅ ጎረቤት አገር እንዳይኖራት** እና ከሚጠሏትና እንድትጠፋ ከሚፈልጉ አገሮች ጋር በመተባበር ስምምነት በመፍጠር ቅራኔን ያባብሳል።
9. **ኢትዮጵያ የተዋዋለቻቸውን ውሎች** ያፈርሳል። ያካበተቻቸውን ሃብቶችና ቅርሶች ይዘርፋል፣ ይሸጣል አሳልፎም ለውጭ አገር ይሰጣል።
10. የአገሪቱ ለም መሬት በተለይም በምዕራብ **ኢትዮጵያ** እየተሸነሸነ ለሱዳን መንግሥት እየተሰጠና ኗሪው ኢትዮጵያዊ በግፍ እየታሰረ እየተገደለ ይገኛል።
11. **የአገሪቱ መሬት በሙሉ በሕዋሓት መንግስት ተብየው፣** የካድሬዎችና የወያኔ አባላት ነው። ለም መሬት ለውጭ አገር መንግሥታት በዶላር እየቸረቸረ፣ እያጫረቱ እየሸጡት ነው። ኑ ኢትዮጵያን ግዙ የኢትዮጵያ ለም መሬት በርካሽ ዋጋ በገንዘብህ የፈለግከውን ለም መሬት መጠኑ ሳይወሰንብህ ግዛ በማለት የመሬት ሽያጭ ንግድ በአዋጅ ሲያስተዋውቅ በአንድ ጋዜጣ ላይ እንደታየው እንዲህ ይላል። "There is no crop that doesnot grow in Ethiopia. Every body is coming" ትርጓሜ "በኢትዮጵያ ውስጥ የማይበቅል የእህል ዓይነት የለም... ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያን ለመግዛት እየመጡ ነው። በአንፃሩ ግን ኢትዮጵያ በዓለም ሕብረተሰብ ፊት በረሃብና በልመና የታወቀች ነች። አፈሯ በፈረንጅ ጫማ እንዳይሄድ ያደርጉ የነበሩባት አገር ዛሬ ለሚጠሉን ሳይቀር ተሸጠች ተቸረቸረች።
12. **የሕዝብ ንብረት** በትግራይ መቋቋሚያ ድርጅት ሥር (በአዜብ የሚመራ) ነው። አገር በአገር ላይ (a state in a state) ተወረን እየተበዘበዝን፣ እየተቀማን እየሸጥን ነው። የህንፃዎች መቆም፤ መብዛት ለሚራበው ሕዝብ ምን ጠቀመው ምን አደረገለት?
13. የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር ወያኔ ትግራይን በነፃ አውጪነቱ ከኛ ውጪ ናቸው ካለ በኋላ **ኢትዮጵያን ገዥነቱ እኛን ተቃርኖ ነው።** እኛ ልዩ ነን። ተዋግተውን ተወረን

የታያዝን ነን። የኢትዮጵያ የጦር ኃይል አዛዥ ጄኔራሎች የወያኔ አባላት የአድዋ ትግራይ ሰዎች ናቸው። ለከፍተኛ ትምህርት እድል የሚሰጠውና፣ የጦር ኃይሉ የሚመራው ከዚያው ትግራይ የሚሆነው ከዚህ በመነጨ አሳብ ነው።

14. **የወያኔ አስተዳደር የሚጠላትን አገርና ሕዝብ እየገዛ፣ ሕዝቧን በድህነት፣ በርሃብ፣** በርዛት፣ በበሽታ እያሰቃየና እየጨቆነ ለመግደል፣ በማሳደድ በህገወጥ እስር ቤት ሊጨርሰን እንደተዘጋጀ እናያለን። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ 15 ሚሊዮን በላይ በአእምሮ በሽታ፣ በርሃብ 10-12 ሚሊዮን በውሃ በሽታ የሚሞተው ሕዝብ ስፍር ቁጥር የለውም።

ከዚህ የበለጠ ምን ሊያደርስብን ይችል ይሆን? ይህ ከዚህ በላይ ከብዙ በጥቂቱ ዋና ዋናውን ለማስታወስ ያህል ነው የጠቀስኩት ለአንድ አገር ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ላለች በነፃነት የኖረችና ለሌሎችም ነፃነት፤ በአርአያነት በአጋዥነት የቆየች አገር ይህ በጣም አሳዛኝ፣ ግፍና መከራ ነው። እኛን ልጆችዋን ሊያስቆጣን ሊያናድደን ቁጭትና ከንፈር መንከስም ውስጥ ሊያስገባን መቻል አለበት። እኔን አናዶኛል አበሳጭቶኛል። ኢትዮጵያ ከኛ ከልጆችዋ ሌላ ማን ሊደርስላት ነው? መናደድ ተገቢ ነው! የሰው የእንስሳም ባህሪ ነው። ለመኖር ትግል ነፃነት ነው።

ይህን የወያኔ ፀረ-ኅብረተሰብ ተግባር መፍራት፣ መጨነቅና መፍትሔውን መሻት የኢትዮጵያኖች ተግባር መሆን አለበት። ተደፍረናል፣ ተዋርደናል በታሪክ የወረሰነው የቀደምት አባቶች ወኔ ባህሪና ተግባር አጥተናል፤ አልያዝንም። የአገር አለኝታን የወረስነውን ቅርስና ሃብት ታሪክ፣ አንድነትና ኩራት በዜግነት ግዳጅነትና ኃላፊነት ለትውልድ ለማስተላለፍ እንነሳ።

Emotions are reaction to an object, not a trait. They are object specific. You show your emotions when you are angry at some one, afraid of something. Emotions come from “heart” not from “head”.

ያልገባን ምንድነው ያልተረዳነው
ይህን ያህል ጊዜ ብዙ የምንለው
በኅብረት የኖርክ ተከባብረህ አብረህ
ታሪኩ የጋራህ ኢትዮጵያዊ ሆነህ

በዘር፣ ቋንቋ፣ ጎሣ ሲለይ አንድነትህ
ብሔር በብሔር ላይ አናክሶ እያጣላህ
ለያይቶ አስቀምጦ ይህ አለው ይህ የለህ
እያበላለጠ ያነሰና በዛህ
ከፋፍሎና አዳክሞ ሲረገጥ ስብዕናህ
ምነው ወኔ አነሰህ ለብቻህ ሲገልህ
ኅብረት አንድነትን መፍጠሩ ተስኖህ
መኖር የጎደለው ነፃነት ተነፍገህ
ሀብት፣ ቅርስ፣ መሬት አገርህን ተነጥቀህ
የሙት ኑሮ እየኖርክ ካሉት በታች ሆነህ
ምንድነው ዝምታው ትዕግስቱ ያልገባህ
ሰው ሆነህ እንስሳ በእጅጉ የዋህ
በስቃይ የምትኖር እንደዚህ ተዋርደህ
ትዕቢት ግፍ ጭቆናው ቢያንገሸግሽህ
አሻፈረኝ ብትል ተናደህ መሮህ
በጣም ብትቆጣ እጅግ አምረህ
ከንፈርክን ብትነክስ ቢጋጭ ጥርስህ
የሰው የእንስሳም ዓይነቱ ባሕሪህ
አግባብ ያለው ሥራ ይህን ማድረግህ
ለመኖር ዋስትና ለማግኘት ፍትህ

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያኖችን ለዘመናት አስተሳስሮ ያኖራቸው ተስፋ፣ ያቆያቸው ፍላጎት ያበረታታቸው የሃገር ቃል ኪዳን እምነት አጎልብተው የአእምሮ ዝግጅታቸውን አነቃቅተው አንገትን ቀና አድርገው በዛሬ ላይ ነገን አይተውና ተመልክተው የተሻሉ ሆነው ለመጭው ትውልድ ማንነት ኩራትና ተግባሮች ሆነዋል። ይህን ማወቅና ማመን፣ ማስቀደም ይገባናል የምንለው መብታችን የምናምን ከሆን ለማስፈጸም የስነ ልቦና የሞራል ዝግጅትና እውቀት ይዘን መነሳት አለብን።

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የሚኖሩበት መንግሥታዊ ሕግ አክብረው ያሰራርና የእምነት ሥርዓቱን ባህላዊ አስተሳሰብ ተከትለው መኖር አለባቸው። ነገር ግን ግፈኛ

ወይንም ጨቋኝ ሕግና ሥርዓት ተሸክሞ ከመኖር ከሱ ነፃ ለመሆን አይደርሱ ቅጣት ቢደርስባቸው የሚመርጡ ግለሰቦች በየቦታውና በየጊዜው ይፈጠራሉ። በግፍና በጭቆና ላይ እንዲቆጡ እንዲያምጹ ለተጨቆነውና ለተበደለው ሆነው የሚፈጠሩ አሉ።

ዛሬም በአገራችን ችግሩና ብሶቱ የወለዳቸው ወደ 92 ፓርቲዎችና ድርጅቶች ይገኛሉ አብዛኛው አገር ወገንን ከዚህ ግፈኛ ወያኔአዊ ሥርዓት ለማውጣት ነው። በአንፃሩ ግን ጥቂቶች ደግሞ ሥርዓቱ የወለዳቸው የባንዳ ባንዳዎች ከትግራይ ብቻ ሳይሆን ከየብሔሩ በስመ ፓርቲ በቋንቋ ላይ የተመሰረቱ፣ ለመሾም፣ ሃብት ለማግኘት ደህንነታቸውንም በወያኔ ያሚያስጠብቁ የነጋዴ ፓርቲዎች አሉ። ይህ የማይካድ ሃቅ ነው። በአብዛኛው የኢትዮጵያን አንድነት የመላው ኢትዮጵያን ብሔራዊነት፣ ዳር ድንበሯን ለማስከበር የሚታገሉ የጊዜው ሃቀኛ አርበኞች አሉ። በታሪካችንም እንደምንረዳው "**እኔ ሞቼ መጪው ትውልድ፤ አገር ትኑር**" ብለው ሕይወታቸውን የሰጡ እንጂ እሾማለሁ እሸለማለሁ፣ ባለሥልጣን፣ ሃብታም እሆናለሁና ለመሆን አስበው አይደለም። ሰው ቤቱን፣ ዘመዱን፣ ሃብቱን ደህንነቱን አሳልፎ መስጠት ለአገር ወገን ፍቅርና ክብር ነው። ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት እየሰጡ ያሉት ዜጎች የሁላችን የጋራ ታሪክ ነው ብለን መቀበልና ማክበር ከጎናቸውም መቆምና መረዳት ማበረታታት ይኖርብናል።

እኛ ዜጎችዋ ይህን ሁሉ ገምግመንና አገናዝበን ሀቅና እውነቱን በመረዳት ትክክለኛ እውቀትና እምነት አዳብረን አገር ውስጥ መልካም ዓላማና ራዕይ ይዞ የሚታገለውን ፓርቲ መርዳት የወያኔን ጥፋት ዘመን ያሳጥረዋል ብዬ አምናለሁ።

ስለዚህ ሰፋ አርገን በአንክሮ ተመልክተን የእያንዳንዱ ፓርቲ ራዕይ ተልዕኮ ዓላማና ግብ (Organizational Behavior) ድርጅታዊ ባህሪ ስትራቴጂና ታክቲካዊ ሥራና ተግባሩን መረዳት ያስፈልጋል።

ይህን ሳያጤኑ በቂ እውቀትና እምነት ሳይዙ ፓርቲዎችንና መሪዎችን በአሉባልታ መፈረጅ፣ አጥፊ ቡድን አድርጎ በማየት ለአገር ወገን እንደከዱ ለጠላት እንዳጎበደዱ፣ ጉያ እንደገቡ አስመስሎ መኮነን፣ መፈረጅ ጠላትን መጥቀም ነው። የሚታግሉትን ማዳከም፤ እንዳይሰሩ ተስፋ ማስቆረጥ፤ ከዚህም አልፎ የራሳችንን አላዋቂነትና ደካማነት ለአገር ወገን አለመቆርቆርን የሚያሳይ ይሆናል።

የምንሰራ እንጂ የምናወራ፤ የምናውቅ ጥበብን የምንቀስም እንጂ በአጉል ዘመናዊ ትምህርት፤ ጥራዝ ነጠቅ በእምነትና በስሜት የፈረንጅ ልጆች ሆነን፤ የአገራችን ኢትዮጵያን የወደፊት ዕድልና፤ የመጪው ትውልድን ዕጣ ማንነት መሸርሸር የለብንም። *በተፈጥሮ ይሁን በጸጋ የኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ ስር መሰረቱን፣ ማንነቱን፣ ተምሮና አውቆ፣ በባህል፣ በወግና በኑሮ ሥርዓት የባዕድ ጥገኛ ሳይሆን የራሱን ተምሮና መርምሮ የሚያይ፣ እያሻሻለ፣ እያደሰ እያሰመረ የዚያ ባለቤት በመሆኑ የሚኩራ፣ የሚመካ ራሱ ተከብሮ አገሩን የሚያስከብር ትውልድ መሆንና ኢትዮጵያዊ ትውልድን ማነጽ የታሪክ፣ የትውልድም ኃላፊነትና ግዴታ፣ እምነት፣ ኅብረተሰባዊ ኮንትራት (Social Contrat) አለብን።*

ኢትዮጵያዊ ነኝ ለማለት በኢትዮጵያ መሬትና ከኢትዮጵያኖች መወለድ በቂ አይደለም። *ኢትዮጵያዊ የሚያደርገን ከጥንት ጀምሮ ትውልድ እያለፈ ትውልድ ሲተካ እየተወራረሰ ሲወርድ ለመጣው ባህላዊ ድርጊቶችና በሁሉም ልብ የሚፈጥሩት ውስጣዊ የጋራ ስሜት የሚገለጽባቸው የኢትዮጵያ ብቻ የሆኑ የጋራ ስሜት፣ የጋራ ሕይወት በመንፈሳቸው በምኞታቸው፣ በስሜታቸው፤ በጠባያቸው፤ በአስተሳሰባቸውና በስራቸው ከሌሎች ሁሉ ለይቶ ኢትዮጵያውያን አሰኝቶ ያኖረን ያቆየን ነው። ይህ ነው ኢትዮጵያዊነታችን (ኢትዮጵያ እኔ ነኝ ጽሑፌ ላይ ወደፊት ያነቡታል)*

ሰው ከእንስሳ የሚለየው አንዱና ዋናው ሰው *ታሪክን* ይሰራል ። *ታሪክም* የኅብረተሰብ የአኗኗርና የመኖር መሰረታዊ መንገድና ዘዴውን ተጠቅሞ መልካም *ሥራን* የሕይወት *መምሪያ* አድርጎ እንዲኖር ስለሚያደርግ ነው።

*ታሪክንና የታሪክ* ስመ ጥሩዎችን የምንማረውና የምናነሳው ይህን ተጠቅመን ስለምንኖርና የዚያ ሰው መልካም ስራ፤ የእኛ የመኖር ውጤት ስለሆነ ነው። *ታሪክ* የሰሩት አልፈዋል፣ ሞተዋል አይጠቀሙበትም ተጠቃሚው በሕይወት ያለው ትውልድ ነው።

የእኛ ቀደምት አባቶች መልካም *ሥራ* እኛን ኢትዮጵያኖችን ለዚህ ጊዜ፤ ለዚህ ዘመን አብቅቶ እያኖረን ነው። ያን መልካም *ታሪክ*፣ እምነት አገር ወዳዳዊ መልካም አስተሳሰብን፣ ባህል፤ ወግ የተፈጥሮ ጸጋን እንደያዝን መኖር የሚጠበቅብን የትውልድ ተግባር ነው። ዘመናዊ ትምህርት ስለተማርን በስሜት በእምነት ፈረንጆች ለመምሰል መሞከር አጉል እንጂ ፈረንጆች አያደርገንም። የተማርነውን ሁሉ መሆን አንችልም። ***“ጥበብን አውቆ ራስን መሆን ግን ከአገራችን ጋር አቆራኝቶ የሚያኖረን የዕውቀት ጸጋ ነው።”***

ኢትዮጵያዊነትን የምንማረው፣ የምናውቀው ከወላጅ፣ ከኅብረተሰብ ነው። ለእኔ ትልቅ ትምህርት የሆነኝ ከታሪክ ያገኘኋቸው ሁለት ምሳሌዎችን ላካፍላችሁ። በጣሊያን የአምስት

ዓመት ወረራ ጊዜ ወደ እንግሊዝ አገር (ለንደን) ተሰደው የሚኖሩ አንድ ደጃዝማች መልካም ተግባር ነው። በመንገድ ዳር ቆመው አበባ በመሸጥ በሚያገኙት ገንዘብ ኢትዮጵያ ውስጥ ከጣሊያን ጋር የሚዋጋውን አርበኛ ይረዱ ነበር። ተሰደድኩ፣ የምኖርበት አገር አገኘሁ ብለው ዝም አላሉም ኢትዮጵያዊነታቸውን በተግባር አሳዩ።

ሁለተኛው የሚያስደንቀኝ ሳስበው የሚያስለቅሰኝ ነው። ከጠላት ጋር በውጊያ ላይ ነበሩ የጦር አዝማች በጠላት ተመተው ትልቅ መቁሰል ደርሶባቸው እያሉ አዝማቹ ደጅዝማች አፈወርቅ በአጠገባቸው ያሉ ደጀን ኃይል ወታደሮች መመታታቸውን እንዳያዩ፣ እንዳያውቁ ከእኔ ራቅ ብላችሁ ተኩሱ ብለው ትዕዛዝ እንደሰጡ፣ በጠላትም ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰው ሞቱ ይባላል። ይህ ታላቅ ጀግንነት **"እኔ ሞቼ አገር ትውልድ ትኑር"** ባይ አባት ለመመታታቸው ለመቁሰላቸው ሳይጨነቁ ሌሎች ወታደሮች የሳቸውን መመታት አይተው እንዳይረበሹ፣ ተስፋ እንዳያጡ ያደረጉት የብርታት የቆራጥ አባት መስዋዕትነት ታሪክ ነው። ምን ዓይነት የአገር ፍቅር ነው? እየሞተ ለትውልድ አሳቢ፣ ተጨናቂ ! ይህን ሳስብ በእጅጉ አለቅሳለሁ። እኔ ዛሬ በነዚህ ታላቅ ምሳሌዎች እኖራለሁ እናንተስ?

ታሪክ ማለት ይህ ነው። የሰው ልጅ ምግባር ማለት ይህ ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ ትዕግሥትን፣ እምነትንና ጽናትን ፈታኝ በሆነ ወቅት ትገኛለች። ሁላችንም በብርቱ ሊያሳስበን የሚገባ አገራዊ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያዊነት የሚፈለግበት፣ ኢትዮጵያዊ ማንነት ይዘን ይህን ጊዜ በድል አድራጊነት አልፈን ለመጭው ትውልድ የተሻለ ለማድረግ ራዕይ ካለን፣ ኢትዮጵያዊ ቃል ኪዳን አድሰንና አጎልብተን መነሳት ነው። ኢትዮጵያዊነት እንዲያብብ፣ ሁላችን የድርሻችንን ማበርከት አለብን፣ መንታ መንገድ ላይ ቆመን፣ በችለተኝነት መመልከት ይብቃን።

ኢትዮጵያ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በላይ የሕዝብ ቁጥሯ እጅግ ነው። የተማረው ምሁር ብዙ ነው። የዕውቀት፣ የሰው፣ ገንዘብ ኃይል ይኖራል አለ። ኃይልም ድል ነው። የተማረው ምሁር በአለም ላይ የተሰደደው አያሌ ነው። አገራችሁን እርዱ አስተምሩ ለዚያ ድሃ ጭቁን ሕዝብ ድረሱለት እያልኩ እለምናለሁ አገር ውስጥ ለሚታገሉ፣ መስዋዕትነት ለሚከፍለው ሕዝብ ድርጅትና ፓርቲ አካል ሁኑ። መማር፣ ማወቅ አገር ወገን ለመርዳት ነው። የእውቀት ጥቅሙ ሊሰራበት ለሌላውም ለማካፈል ነው። ለመሆኑ የተማረው ኢትዮጵያዊ ምን እያሰራ ነው? አገር ስትጠፋ አጋዥነቱ የቱ ላይ ነው? የእውቀት አገልግሎት ጥቅሙ ምንድነው? ተጠያቂነቱ የሕሊና ኃላፊነቱ የት ነው? ያልገባን ምንድነው ያልተረዳነው?

በተለይ በውጭ አገር በስደት የምንኖረው፣ ከአገር ከወገን ርቀን ስንከራተት የነበርነው ያለነውም የኢትዮጵያ ችግር ውጤቶች አይደለንም? ዛሬ ብዙዎቻችን ያን ረስተንና ማሰብ እንኳን የማንፈልግ አለን። ሀገር ወገን መውደድ ከዚያም መጠበቅና መንከባከብ የት ነው? አገር ማለት ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያዊነት ታሪክ፣ ባህል የክልሉ ባለቤትና ፍቅር ሲታሰብና ሲጠበቅ ነው።

**"ፍቅር" ሰዎችን ለሰላምና ለፍትህ፣ በድፍረትና በጽናት፤ እንዲቆሙ እንዲፋለሙ የሚያደርጋቸው ልዩ ኃይል ነው።**

**"ነፃነት" ዋጋ ይከፈልበታል። ያለ ትግል ነፃነት ያለ መስዋዕትነት ደግሞ ሀገር ወገን አለኝታ አይገኝም።**

ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ ፓርቲዎችና ድርጅቶች የወያኔን አጥፊነት በደንብ የተረዱና ያወቁ፤ የወያኔ ሥርዓት መወገድ አለበት ብለው ተገንዝበው ይልቁንም *ለመጭው ትውልድ ባዶነትና ባርነትን* ላለማስረከብ የሚተጉና የሚታገሉ ናቸው ብዬ አምናለሁ። የኅብረተሰቡን ርዳታ ይሻሉ፤ ይፈልጋሉ። በሕዝብ ውስጥ ሆነው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል የቆረጡ የዘመኑ ሃቀኛ ኢትዮጵያኖች ሩቅ ማየት የሚችሉ ናቸው። ካሰቡበት ለመድረስ የድል ባንዲራን ለማውለብለብ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተካፍሎን እንደ ጥንቱ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ማሰብና መስራትን ይጠይቃል።

ለነፃነታችን የሚንቀሳቀሱትን፣ እኛን ወክለው የሚሞቱት፣ የሚታሰሩት፣ ለጋራ አገር፣ ለጋራ ታሪካችን ነው ብለን ከጎናቸው ልንቆም በተገኘው መንገድ ልንረዳቸው ይገባል እንጂ አሉባልታ ልናወራባቸው በሆነ ባልሆነው ልንተቻቸው ፈጽሞ የሞራልም ሆኑ የስነ ልቦና ብቃትም እውቀትም አይኖረንም ብዬ አምናለሁ።

ነፃነት ከፍቅር ብቻ የሚመጣ አይደለም። ከትግል ከተግባራዊ አስተዋጽኦ እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የወያኔን ሥርዓት (ወያኔዊነት) ለማስወገድ፣ ኢትዮጵያን ካለችበት መጥፎ የጭቆና የወረራ አስተዳደር ነፃ ለማውጣት በሰላም በዲሞክራሲያዊ መንገድና ሥርዓት እየታገሉ ይገኛሉ።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች የሰላም ትግል የሚያደርጉት የሕወሓት (ወያኔ/ኢህድግን) ሕገ መንግሥት ተብዬውን ተቀብለው በሰላማዊ መንገድ በመንቀሳቀስ ሥርዓቱ እንዲወገድ ለማድረግ ነው። በሰላም እንታገላለን ያሉ በኢትዮጵያ ሜዳ እና በትግሉ ቦታ ለሚገኙ "የሰላም ትግል መሳሪያቸው" መነጋገር፣ ሃሳብ መለዋወጥ፣ መደራደርና በመግባባት ስምምነት ላይ መድረስ ነው።

ይህን መደራደር፣ መስማማት የማይፈልጉና የሰላም ትግሉን፣ በዲሞክራሲያዊ በሕዝብ የምርጫ ድምጽ መሳሪያነት የማያስተገብሩና የማይፈጸሙ ከሆነ ተቀዋሚ ፓርቲዎች አዲስ አበባ ከተማና በሌሎች ውስጥ ምን ያደርጋሉ? በአንድ አገር ውስጥ ሕዝብ ተከባብሮና በሕግ ተዳኝቶ በሰላም ለመኖር ሕገ መንግሥት ያስፈልገዋል። ሕጉም በሁሉም ዜጎችዋ መከበር ይኖርበታል። በአገራችን እነዚህ ሕግጋት ስለ ጎደሉ፣ ስለተጓደለ የሰላማዊ ፖለቲካ እንቅስቃሴውን እያዳፈነው ነው። ፖለቲካ ያለ መርሆ (No Politics with out prinicple) ሊካሄድ ሊፋለም አይችልም። ከሁሉ በፊት ሕጎችና ደንቦች (Policies) መኖር አለባቸው። ይህን መሰረት አድርጎ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲሟሉ እንዲፈጸሙ በሕጉ አኳያ መጠየቅ ማስፈጸም ይሻል። ይህን መሰል መሰረታዊ ሕግጋቶች ሳይኖሩን በህግ ለመጠየቅ ለማሰራት፣ለማጋለጥና ሕጋዊ ሥርዓትን ለማስፈጸም ያዳግታል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን መብቱን የሚያስከብርበት ሕጎችና ደንቦች መሰረታዊ የሕዝብ ኃይል መጠየቂያዎችና ማስፈጸሚያዎች ሆነው መገኘት አለባቸው። የምንፈልገው እና የምንመኘው የምንሻውን ለሕዝብ የሚሆኑ፣ የሚመካበትና የሚሰራበት መመሪያ ፖሊሲ (Policy) ማውጣት፣ መለወጥና መደንገግ አስፈላጊ ነው። ፓለቲካ (Politics) ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው። ስለሆነም በሳይንስ አንጻር እየታየ መመርመርና መገምገም፤ አገናዝቦ መረዳትንም የሚጠይቅ ነው። ይህን ካልያዘ መፎከሪያና የአሉባልታ ሥራ ሆኖ ይቀራል። ፖለቲካ ግቡን ሊመታ የሚችለው መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎችን ሲይዝና አገርን የመጠበቅ የመገንባት መርሆ (Prinicple) አቅጣጫ ሲይዝና ሲኖረው ነው።

ይህም በመሆኑ በአገራችን የሰላም ትግል ተደርጎ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማምጣት የፖሊሲ ደንቦችና የፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ሊዘጋጁና ሕግ ሆኖ ደንቡ በፓርላማ ሊጸድቅ እና አፈጻጸሙ ላይ ስምምነት መደረስ አግባብ ያለው ነው።

መደራደር፣ መስማማት ብሎም መፈራረም አንድ መሆን፣ አንድ ዓላማና ግብ አለን በአንድ ላይ እንሰራለን ማለት አይደለም። በአጭሩ ሕዝብ በምርጫ ድምጹ የሚፈለገውን የወደደውን ያመነበትን ይምረጥና፣ የሕዝብ መንግሥት እንዲኖረን፣ አምባገነን ገዢዎች በሰላማዊ መንገድ፣ ሕግ አክብረው፣ ሕግና ብዙሃን ሕዝቡን ፈርተው ለዚያ ተገዥ እንዲሆኑ ነው። ሕግ የወጣው እንዲፈረም የተደረገው ወያኔን ሊጠቅም ሆኖ አይደለም። ወያኔ ለፈረመበት ሕግ ለተስማማበት የፓርቲዎች ሥነ ምግባር ሕግና ደንቦች ተገዢ እንዲሆን ነው፡ ፡ ውሉን ካፈረሰው አምባገነንነቱን በሕዝባችን በአለም ኅብረተሰብ ፊት ለማጋለጥ ነው።

የሥነ-ምግባር ሕግ ተረቆና ስምምነት ተደርሶ መፈረሙና ሕግ ሆኖ ለመውጣቱ የመላው ኢትዮጵያዊ አንድነት ፓርቲ ባደረገው ከፍተኛ ጥረትና አስተዋጽኦ ነው። ወያኔን በወያኔ ሥርዓት ላይ ይህን መሰል ሕግ ማምጣት፣ ማስደንገግ ትልቅ ታሪካዊ ምዕራፍ ነው። ይህ የሰላም ትግል ዋና መሰረት ነው ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል እንዲሉ (Win starts at the beginning) በዚህ መነሻ መኢአድን ሁላችን እውነተኛ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ የምናስብ የምንቆረቆር ልንደሰትበት፤ ልንኮራበት በቻልን ያስፈጸሙትን ልናደንቃቸው፤ ልናከብራቸው ልናበረታታቸው ይገባ ነበር። ግን በአብዛኛው በተለይ በውጭ ካለው ከተማረው ይህ ባለመታየቱ አዝናለሁ። ጊዜና ትውልድ ይፋረዳው ነው።

የወያኔን አምባገነናዊ ባህሪው ተግባሩን የሚያስቆም ፖሊሲ ሕግ ሆኖ መውጣት ለምን አጠያያቂ እንደሆነ አልገባኝም? የወያኔ መሪ አቶ መለስ ይህን ስምምነት የፈረመው ፈልጎት ይጠቅመኛል ብሎ ሳይሆን ተገዶ ነው። የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ በሰላም መንገድ ትግልን በሕግ ላይ አስመርኩዞ ደጋግሞ በአለፈው ምርጫ (97) ላይ የጠየቀው በሕግ መንግሥቱ ውስጥ የተደነገጉ በተግባር እስራ ላይ ይዋሉ ነው። መኢአድ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለኢትዮጵያ አንድነት መረሆ ላይ የቆመ ሕግን የሚሻ ነው። ወያኔም ይህን በመረዳት አምባገነናዊነቱን ለመሸፈንም ይሁን በእምነት የፓርቲዎች ሥነምግባር ሕግና ደንብ ሆኖ እንዲጸድቅ በውጭ አገር ታዛቢዎች ፊት ፊርማውን አስቀምጧል። ውልን ማፍረስ ሕገ ወጥነትን ብቻ ሳይሆን ሕዝብን የሚያስቆጣና አመጽንም የሚያስከትል ይሆናል። በዓለም ኅብረተሰብ ፊትም የሚያጋልጥ እና ብሎም ለፍርድ እንደሚያቀርብ ይታወቃል።

መኢአድና የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን በደንብ ያውቃሉ። በወያኔ ፊርማና ቃል ዋስትና አያሻም፤ እምነትንም አያጠናክርም። ነገር ግን በሰላማዊ ትግል ይህ አስተዳደር ይነሳል ብለው ያምናሉ። የአቶ መለስ ፓርቲ ግን ባልፈረምን ዓይነት ቁጭት የሚታይበት ይመስላል። ወያኔ አጥፊነቱን የሚያውቅና መጠላቱንም በእጅጉ የተገነዘበ በመሆኑ ከስልጣን እንወገዳለን ብሎ በእጅጉ ፈርቷል። ከወዲሁ ሰውን ማስጨነቅ፤ ማሰርና መግደል፤ ምርጫ ካርዶችን መንጠቅና መስረቅ፤ ምዝገባን ማፈንና ማወክ ተጀምሯል። ለሕዝብ የፓርቲዎች ክርክር ለ ጥያቄና መልስ የማይቀርብበት ነው። የገዥው ፓርቲ ወያኔ ለክርክሩ በአብላጫ ብዙ ደቂቃዎች እንዲሰጠው በማድረግ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በላይ አግኝቷል። ይህ ሕግ ያልተከተለ ለመሆኑ መኢአድ ከክርክሩ ራሱን አግሏል። ተገቢም ነው። ማንኛውም ፓርቲ በፓርቲነት ለምርጫ ተወዳዳሪ በሕግና በሕዝብ ፊት እኩል ነው። አብላጫ ደቂቃዎች

ይገባኛል ብሎ መጠየቅ ሕግንና ፓርቲዎችን፣ መፈታተን ይመስላል ማነው ጠንካራ ሕግ እንዲከበር የሚጠይቅ? ወይንም ማነው ዳካማ የሚል የትግል ስልት ነው። መኢአድ በዚህ ሕጋዊ ተግባር፣ ድፍረትና አልበገር ባይነቱን፣ ለዓላማው ያለው ጥንካሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ እየሆነ ነው።

ይህ ያልገባችሁ በመኢአድና በመሪዎች ላይ የስድብ ናዳ፣ ርግማን ያወረዳችሁ ወያኔን እየጠቀማችሁ እንጂ ኢትዮጵያንን አይደለም። መልካም ልቦና ጥሩ አስተያየትን አምላክ ይስጣችሁ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ የትውልድ ኃላፊነትና ግዴታን ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ደህንነት፤ አለኝታን መሰረት አድርጎ ዓይነተኛ ራዕይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊነት፣ እኩልነት፣ ሉዓላዊነት እንዲጠበቅና ሊያፈርስ የመጣውን ወያኔ/ኢሕድግን ከስልጣን በሰላማዊ መንገድ እንዲነሣ የሚታገል ሕብረ ብሔር የሆነ ፓርቲ ነው። መኢአድ የሰላም ትግልን የሚያካሄደው ኅብረተሰብን በማቀራረብ፣ በማቻቻል የሰለጠነ ውይይትን፣ መነጋገር፣ መደራደርና ስምምነትን መርሆ አድርጎ የዲሞክራሲ የጋራ ስምምነት ቃል-ኪዳን በከፍተኛነት አጽንቶ ነው። የሕዝብን ድምጽ በምርጫው ተቀብሎ ወደ ሰላማዊ የሕዝብ መንግሥት መሸጋገር የዲሞክራሲ ባህላዊ ሥልጣኔ እንዲሆን በመሻት መኢአድ ከፍተኛ ትግል እያደረገ ይገኛል። መኢአድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፖለቲካዊ፣ ከኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ በደል ነፃ ሆኖ ፍትሐዊ አስተዳደር እንዲገኝ ለረዥም አመታት በማያወላውል አቋም ጸንቶ እየታገለ ነው። በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ክፍሎች ሁሉንም ብሔረሰቦች በእኩልነት ያካተተና የታቀፈ ሰፊ መሰረት ያለው የሕዝብ ስሜትና ፍላጎትን የሚያንጸባርቅ፣ አመኔታቸውንም ሊያተርፍ የሚችል በሊበራል ዲሞክራሲ ላይ የተመሰረተ (መኢአድ) ፓርቲ ነው። የዜጎችዋን ሁሉ እኩልነት፣ የጠረፉን ጥብቀትና የወደፊት ዕድሏን ብሩህነት ለማረጋገጥ የዜጎችዋን ሁሉ ተሳትፎ የሚጋብዝና የሚያበረታታ በቋንቋ ብሔር ጎጠኝነት ላይ ያልተመሰረተ፣ የፖለቲካ ሥርዓት መስፈን አማራጭ የሌለው ስለሆነ ኢትዮጵያን ከመፈራረስ በማዳን መኢአድ ዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያን ይገነባል ብዬ አምናለሁ። ከጎኑም ልንቆምለት የሃቀኛ ኢትዮጵያዊነት ወቅት ነው።

መኢአድ ሕዝብን ከጎኑ በማሳለፍ በጥንካሬና በቆራጥነት በመንቀሳቀስ ትግሉን በስፋት በማፋፋምና በማያያዝ ለ2002 ብሔራዊ ምርጫ ዝግጅት ላይ ይገኛል።

ዲሞክራሲ ዋና ከፍተኛ የሕዝብ መንግስት ማመንጫ የሕግ የበላይነት፣ የመብትና የእኩልነት ሥርዓት መምጫ የሕዝብ መሳሪያ ነው። ለውጥ ለማምጣት የሕዝብ ተሳትፎ በጋራና በስፋት ያስፈልጋል። ዲሞክራሲያዊ የሰላም ትግል ዋና ማሸነፊያ መሳሪያው የሕዝብ ምርጫ ነው። ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ አስፈላጊ ለመሆኑ ግልጽ ነው። ብዙ ብሔር- ብሔረሰብ ያላት አገር ዲሞክራሲን በእጅጉ ትፈልጋለች። የዲሞክራሲን ስርዓት ምርጫን ማቋረጥ ዲሞክራሲን መግደል ነው። የምርጫ ሜዳን ሁሉ ለወያኔ ለቆ መተው የትግል ስልት ካለመሆኑም በላይ ፀረ- ዲሞክራሲ ያደርገዋል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተገኘ ምርጫ ሁሉ መሳተፍ አለባቸው። አለመሳተፍ፣ ከሕዝብ ምርጫ መውጣት ከሕዝብ ይለያቸዋል። ለሕዝብ መቆማቸው ፓርቲ መሆናቸው ይቀራል። ለመምረጥ የተዘጋጀ ሕዝብ አለ። የተጀመረ የሕዝብ ተሳትፎን በከፍተኛ ያሳየ የግንቦት 97ቱ ምርጫ ለዚህ ዋና ተመክሮአችን ነው። ነገር ግን ወያኔ በአምባገነንነቱ ይህን አይፈልግም። ከሆነም ተወዳዳሪዎቹ በዘር ቋንቋ ላይ የተደራጁ ቢሆን ይመርጣል። በዚህ ሁኔታ የተደራጁትን በተመሳሳይነታቸው አይፈራቸውም ለመወዳደር ቢገቡ ይጠቅመዋል። የኢትዮጵያ አንድነት፣ ኅብረ ብሔርነት ያለው ያስፈራዋል በምርጫ እንዳይገቡ ሕገ ወጥ ተግባራትን ይፈጽማል፡ ስማቸውንም ማንሳት አይፈልግም።

የወያኔን አስተዳደር ለማስወገድ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ያስፈልጋል። በሰላም በሕጋዊ ሥርዓት የወያኔን አስተዳደር ለማስለቀቅ የሕዝብ ምርጫ ኃይል ያሻል።
ተቀዋሚ ፓርቲዎች በምርጫ በአሸናፊነት፣ በድል አድራጊነት ለመወጣት በጥንካሬ ተደራጅቶ መንቀሳቀስን፤ ያሉበት ሁኔታን ያገናዘቡና የአሰራር ብቃትን፣ የዓላማ ጽናትን ለትግል ቁርጠኝነትን፣ ሕዝብን በስፋት ያቀፉና ያካተቱ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው።

የምርጫ ፓርቲ ነኝ ብቻ ሳይሆን ለማሸነፍ ተግቶ ለቆመለት ራዕይ በጥንካሬው ጸንቶ በአልበገርነት፣ ለወያኔ አሳልፎ የማይሰጥ መሆኑን ለመራጩ ሕዝብ ማስተማመን ይኖርበታል፡ ምርጫ ያለ ተቃዋሚ ፓርቲ(ዎች) የወያኔ ብቻ ተሳትፎ ፀረ-ዲሞክራሲና አምባገነናዊነት ነው። ምርጫው በነፃና በፍትሐዊ ሥርዓት በፓርቲዎች ሥነ ምግባር ሕግን አክብሮ ቢከናወን ጠቀሜታውና አሸናፊነቱ የተቋዋሚ ፓርቲ ነው (መኢአድ) ነገር ግን ምርጫው ነፃና ፍትህ የጎደለው ቢሆን ከምርጫ በፊት ሁከትን ሰላምና ደህነትን ያደፈረሰ ከሆነ ወያኔ ገዥው ፓርቲ የፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ውልን እንዳፈረሰ ሆኖ ፓርቲዎች በተለይ መኢአድ ለመራጩ ሕዝብና ለዓለም ኅብረተሰብ ታዛቢዎች አሳውቆ ምርጫውን ባይሳተፍ እንኳን አሸናፊነቱ እውን ይሆናል። ከምርጫ በኋላም ቢያጭበረብር እንደ ልማዱ ኃይልን ተጠቅሞ ማሰር፣

ማዋከብን በአደባባይ መግደልን ቢያሳይ ሕዝብን ለአመጽ መጋበዝ በመሆኑ ፀረ-ዲሞክራሲያዊነቱና አምባገነንነቱን በገሃድ በዓለም ኅብረተሰብ ይጋለጣል። ትግሉም ወያኔ እስካልተነሣ ድረስ ይቀጥላል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች መኢአድ በራዕዩ ጸንቶ ለውጤቱም መሠረት ያለው ሊቋቋም የሚችልበትን ብልህነት የተሞላበት ስልትን በመንደፍ፣ ለህዝብ ግልጽ በመሆን፣ እምነትን አሳድሮ ሕዝብን በቆራጥነት ከጎኑ ማሰለፍ ይኖርበታል። ነፃነት የተጠማን ሕዝብ ምን ኃይል ያቆመዋል። ሕዝብ የናፈቀው ኅብረትና አንድነትን አስተባብሮ ለድል መብቃትን ነው።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁሉ ኃይላችሁን በማቀራረብ ኅብረተሰብን በማቀፍ ዋና ተቀዳሚ ተግባራችሁ "ሃገር ማዳን" የግባችሁ ስምምነት <u>ወያኔን ማስወገድ</u> ሆኖ የሕግ የበላይነት ዲሞክራሲያዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ለማምጣት ጊዜን ገደብ አድርጎ (Fight to Win) ትግል ለማፋፋም ይሁን።

የፓርቲዎች ዓላማና የትግል ስልት እንደ አመሰራረታቸው ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ ልዩነት ይኖራል። ነገር ግን ልዩነትን አቻችሎ አገርን ከጥፋት ማዳን ዋና ተግባር እንዲሆን ለግለሰብ ወይንም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ኃይልን ማዋል የአገር ታሪክ መሆኑ ቀርቶ የግለሰብ ታሪክ ማኅልበት ስለሆነ በጽኑ መተባበር ያለበት የአገር አንድነትን፣ ዳር ድንበርን፣ የሕዝብ ሰላምና ደህንነት ለማስከበርና ለመጠበቅ መሆኑ ነው።

በወያኔ ሥርዓት ውስጥ ያሉ የሥርዓቱን አገር አጥፊነት፣ ፀረ-ኅብረተሰብ መሆኑን በማስገንዘብ እንዲከዱ ማድረግ፤ የወጡትንም ተቀብሎ የትግሉ አካል ማድረግ መልካም ነው፡

ወያኔ በትግራይ ክፍለ ሃገር የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት ሆኖ የኢትዮጵያ አንድነትና ኢትዮጵያዊነትን ተቃርኖ እያስተዳደረ እያጠፋ ነው። የትግራይ ተወላጆች በትግራይ ተወለዱ እንጂ ኢትዮጵያዊነታችሁ አጠያያቂ አይደለም። ትግራያን ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ማን ይሆናል? ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ስትሰብኩ ኖራችሁ ዛሬ ከኢትዮጵያ ተለይቶ የትግራይን መገንጠል ትቀበላላችሁ? ትጠይቃላችሁ? እንዴት? ታሪካችንን፣ ቅርሳችን፣ ሃብታችንን እምነታችንን ስሜታችንን ማንነታችን የጋራ በመሆኑ እናንተ በታሪክ ሁለንተናዊነት የኢትዮጵያ ልጆች ናችሁ። አሁን ግን በዝምታም ይሁን በጥቅም የምትታገለግሉት ለወያኔ ነው።

ዛሬ በወያኔ ሥርዓት በንዋይነት ህሊናችሁን ሸጣችሁ የምታገኙት ጥቅም፣ ድሎት፣ስልጣን ሃብትና ትምህርት በሀቅ ለእውነት ብትቆሙ ነገ በኢትዮጵያዊ መንግሥት በአገር አንድነት ኅብረ-ብሔራዊነት፣ በታሪክ ትውልዳዊ ኩራት በአስተዋጽኦ ብቃታችሁ ታገኙታላችሁ።

የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ የኢትዮጵያን አንድነት ማስከበርና ብሎም መጠበቅ የትውልድ፣ የታሪክ ግዴታና ኃላፊነት በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠበቅበት ነው። ታሪካችንን አገናዝቡ፣ መርምሩ በዓይነ ሕሊና ለማየት ሞክሩ (ዓፄ ዮሐንስ)። አገር በወያኔ ተወራ ስትበዘበዝ በዝምታ፣ በትዕግሥት ወይንም *"የአባትህ አገር ሲወረር አብረህ ውረር"* ዓይነት ሆኖ አኩሪ ታሪክ የነበረንን ችላ ብሎ መተው በታሪክ ትውልድ የሚያስጠይቅ ትልቅ የታሪክ ጠባሳ እንዳይሆን ከወዲሁ ለዚህ ትግል በመቆም አጋርነታችሁ ይታይ።

የኢትዮጵያ የጦር ኃይል፣ የፖሊስ፣ የዳኝነት እንዲሁም በተለያዩ ሙያዎች ተሰማርታችሁ የምትገኙ ሁሉ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ አካል የሕዝብ አገልግሎት ሰጭዎች፣ የአገር ዳር ድንበር አስከባሪዎች፣ የሰላምና ደህንነትና የፍትሕ ጠባቂዎች ናችሁ። የአገር ነፃነት የህግ የበላይነት የሕዝብ እኩልነት ፍትህ ሰላምና ብልጽግና በአገራችን ቢኖር ቢጠበቅ የሁላችን ኢትዮጵያዊ ተጠቃሚነት ደስታና ኩራት ነው። የዜግነት ግዴታችሁና ኃላፊነታችሁ ትውልድ የሚጠበቅበት መሰረታዊ ታሪክ እንደ ሰራችሁ በእናንተ ጎልቶ የሚታይ ስለሆነ ዛሬ አገራችሁ ላለችበት ሁኔታ ከሌላው ሁሉ በተለየ ከእናንተ በእጅጉ ይጠበቃል። በሕግ መንግሥቱና በፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ላይ የተደነገጉ ሕጎችና ደንቦች በሥራ ላይ እንዲውሉ ወገናዊነት በማይታይበት ሁኔታ እንዲተረጎሙ የበኩላችሁን እንድታደርጉ ኅብረተሰብ ይጠብቃል። ሃቀኛ የቁርጥ ቀን ኢትዮጵያዊነት ይፈለጋል።

የኢትዮጵያ ዳር ድንበር፣ አንድነት አስጠብቆ የመልካም አስተዳደር ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የዜጎችዋ ሁሉ አስተዋጽኦ እጅ ለእጅ ክንድን አስተባብሮ በመነሳት ልንፈላለግ፣ ልንጠራራ ጊዜው አሁን ነው።

***...."የእኔ ታሪክ ያበቃል የእናንተ ታሪክ ከዚህ ይጀምራል የኢትዮጵያን አንድነት በመጠበቅ ዳር ድንበራችሁን ማስከበር ካልቻላችሁ ያን ጊዜ የእናንተ ታሪክ ይሞታል የእኔ ታሪክ ደግሞ ያን ጊዜ ይጀምራል።".... ቀ.ኃ.ሥ.(1967)***

ኢትዮጵያ ያገጠሟት ችግሮች ሁሉ በድል አድራጊነት ተወጥታ ዜጎችዋ ሁሉ እንደ ጥንቱ ኢትዮጵያ ሲኖሩባት የምታስደስት ርቀው ከሀገር ውጭ ሲሄዱ ትዝታዋ ተመልሰን እስከምናያት የሚያስቸኩለን፣ የምታጓጓ፣ የምትናፈቅ አገር እንደምትሆንም ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ። በቅርብ ጊዜም የዚህ ድል ባለቤት ትሆናለች። ይህን እውን ለማድረግ ሁላችን ይህን ተረድተንና አውቀን ተሳትፏችንን በተግባር ለማሳየት እንድንችል በማለት ይህን ጽሑፌን ***ያልገባን ምንድነው ያልተረዳነው?*** በሚል በአንድ ርዕስ በሦስት ዋና ክፍሎች ላይ በማተኮር ለመጻፍ ያነሳሳኝን ከሞላ ጎደል "ነገር ቢያበዙት በአህያ አይጫንም" ለብልህ ሕዝብ ብዙ አይነገሩም ነውና አሳቤን እንደምትረዱልኝ በመተማመን በዚህ እደመድማለሁ።

ኢትዮጵያ ሕያው ነች
ኢትዮጵያ ታብባለች
እግዚአብሔር ከኛ ጋር ይሁን።